#የአሳሞች_ዕድር!

•

በደርግ ዘመነ መንግስት ወጣቱ በቀይ ሽብር ገነፈለ። ባለራዕዩ ጀነራልም ወጣቱን ሰብስቦ የነፃነቱን ትግል ለኮሰ። በእርግጥ ወጣቶቹ ከደርግ መንግስት ነፃ የወጡት ባለራዕዩ ጀነራል ህይወት ካለፈ በኋላ ነበር። ወጣቶቹ የደርግ መንግስትን አስወግደው የኢህአዴግ መንግስት መሰረቱ። የሚተዳደሩባቸውንም ህጎች አፀደቁ። ተገዢ ለመሆንም ቃል ገቡ።

ህጋቸው በሙሉ የነበረው የደርግ መንግስት የሆነውን ነገር መፀየፍ ነበር። ነገር ግን በተንኮል ላቅ ያሉት ለስልጣን መራኮት ጀመሩ። በመጨረሻም ጠ/ሚኒስቴሩ ስልጣን መንበሩን ተኮናተረ። ጠ/ሚኒስቴሩ በቅድሚያ ያደረገው ነገር የደርግን ስራዎች መደምሰስና እንደ አዲስ መጀመር ነበር።

ከዛ የደርግ መነሻ ሀሳብ የነበሩትን የአባይ ፕሮጀክት ኢህአዴግና የኔ ነው ሲል አስተዋወቀን። በህዝቡ ላብና ጉልበት መገንባትም ተጀመረ። የግድቡን ከፍተኛውንም መዋጮ መዝረፍ ጀመሩ። ድልብ ሐብታምም ሆኑ።

በመጨረሻ ወጣቶቹ የሰበዓዊ መብት ጥሰቶችን፣ ግድያውን፣ አፈናውን፣ ስደቱን ሲመለከቱ አይናቸውን ማመን አቃታቸው። ደርግ ነው ወይስ ኢህአዴግ ሲሉም ግራ ገባቸው። ግን የቱ የተኛው እንደሆነ ለመለየት ቸገራቸው።

•

"The creatures outside looked from pig to man, and from man to pig, and from pig to man again; but already it was impossible to say which was which."

•

#ደርግ_ወይስ_ኢህአዴግ?

•

ደርግና ኢህአዴግ በአንድ ተደባልቀው
በአንድነት አደጉ በአንድ ህዋስ መሸገው
ይሄው በጉበዝናም በፈቃድ ስህተት
ትርጓሜው አይለይም አንድ ነው በማለት
እፅፋለው ፅፈት እስታለው ስህተት
ደርግ ሲሉኝ ኢህአዴግ፣ ኢህአዴግ ሲሉኝ ደርግ

ኤፍሬም ስዩም (የተሻሻለ)

•

#ቸር_ጊዜ!

#በአንተነህ
#እሁድ ሰኔ ፲፮ ቀን ፳፻፲፩